የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፵፯
አዲስ አበባ ሐምሌ ፰ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 47
ADDIS ABABA 15th July, 2014

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፰/፪ሺ፮ ዓ.ም

ለመጠጥ ውሃ፣ ሳኒቴሽንና ሃይጅን ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ……………………ገጽ ፯ሺ፬፻፵

CONTENTS

Proclamation No. 848/2014

International Development Association Financing Agreement for Financing the Water Supply, Sanitation and Hygiene Project Ratification Proclamation……………………………….. Page 7440

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፰/፪ሺ፮

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለመጠጥ ውሃ፣ ሳኒቴሽንና ሃይጅን ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፩፻፴፫ ሚሊዮን ፪፻ ሺ ኤስ.ዲ.አር (አንድ መቶ ሰላሳ ሶስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ. ኤፕሪል ፲ ቀን ፪ሺ፲፬ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፭ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION No. 848/ 2014

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

WHEREAS, a Financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit in an amount not exceeding SDR 133,200,000 (one hundred thirty three million two hundred thousand Special Drawing Rights) for financing the Water Supply, Sanitation and Hygiene Project, was signed in Addis Ababa on the 10th day of April, 2014;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Financing Agreement at its session held on the 12th day of June, 2014;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለመጠጥ ውሃ፣ ሳኒቴሽንና ሃይጅን ኘሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፰/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ. ኤፕሪል ፲ ቀን ፪ሺ፲፬ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር 5386-ET የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፫. **የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፴፫ ሚሊዮን ፪፻ ሺ ኤስ.ዲ.አር (አንድ መቶ ሰላሳ ሶስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፰ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for Financing the Water Supply, Sanitation and Hygiene Project Ratification Proclamation No. 848/2014".

2. **Ratification of the Agreement**

The Financing Agreement Credit number 5386-ET signed in Addis Ababa on the 10th day of April, 2014 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

3. **Power of the Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount not exceeding SDR 133,200,000 (one hundred thirty three million two hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

4. **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 15th day of July, 2014.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**